# ሩቅ አስቦ ቅርብ ያደረው

አትናቲዎስ ገብረመድህን

08-29-14

እነሆ ሁለት ዓመታት ተቆጠሩ፤ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና ኢትዮጵያ ከተለያዩ፡፡ ኢትዮጵያና ሕዝቧ ግን እሱ ባሰመረው መስመር ላይ መትመማቸውን ቀጥለዋል፡፡ከድህነትና ከተረጂነት፣ ከተመጽዋችነት ለመላቀቅና ራስን ለመቻል ለራስ የበቃ ሆኖ ለመገኘት መሰናክሎችን እያስወገደና እየረመረመ ጉዞው ለብሩህ ሀገራዊ ነገ ቀጥሏል፡ ፡ መሠረቱ ሕዝብ ነውና አንድም ምንም የሚገታው ኃይል የለም፡፡

መለስ ዜናዊ የኖረባቸው 57 ዓመታት በበርካታ ውጣ ውረዶች፣ ፈተናዎችና መሰናክሎች ውስጥ እያቆራረጠ ያለፈባቸው ነበሩ፡ ለግሉ ኖሮ አላለፈም፡፡ ይልቁንም ለታላቅ አገራዊ ዓላማ ተፈጠረ፡፡ ለዚህም ኖሮ ያለፈ ከኖረበት ዘመን በላይ የሰራ፣ የደከመ፣ የታተረ፣ ድፍን አገርን በታላቅ ሥር ነቀል ለውጥ የመራ፤ ባህሪትዋን የቀዘፈ የመርከቡ ካፒቴን ሆኖ ማዕበል እንዳያገኛትም ጠብቆ ወደ ሠላማዊው ውቅያኖስ የመራትና እየመራትም የነበረ ጎልማሳ ሰው ነበር፡፡

የሚወዱትና የሚያከብሩትም፤ አምርረው የሚጠሉትም፤ በጋራ የሚስማሙበት በአንድ የሚቆሙበት እውነት አለ፡፡ ሲበዛ አንደበተ ርቱዕ፤ ተናግሮ የማሳመን ችሎታው የላቀ፤ በራሱ ብቃት የሚተማመን፤ አይቻልም የሚለውን ማንኛውንም አስተሳሰብና አመለካከት በይቻላል ለውጦ የማሳየት የንድፈ ሀሳብም የተግባርም የመሪነት ብቃትና ክህሎትም ያለው ሰው ነበር፡፡

መለስ በሱ ትውልድ ዘመን የነበረው ለውጥ ናፋቂ ኢትዮጵያዊ እንዲሁም በአፍሪካና በኤሽያ በአውሮፓም እንደነበሩት ተራማጅ ተማሪዎችና ምሁራን ማርክሲስት ሌኒኒስት እንደነበር ግልጽ ነው፡፡

የታላላቆቹን የጀርመናውያኑን ፈላስፋና ኢኮኖሚስቶች የካርል ማርክስና የፍሬድሪክ ኤንግልስን፣ የሩሲያውን አብዮተኛ ቭላድሚር ኤሊይች ሌኒንን፣ የቀደምት ፈላስፎችንና ታላላቅ የአውሮፓ ፀሐፍትን፣ የቻይናውን ማኦ ዜዱንግን፣ የነቼዌን ላይንን፣ የላቲን

አሜሪካን ትግል መሪዎች የእነ ፊደል ካስትሮ ሩዝን፣ የነቼጉቬራን፣ የቪየትናሙን ትግል መሪ አጎት ሆቺሚንን የሽምቅ መሪውን ጄኔራል ጂያፕን፣ የቺሌውን ሣልቫዶር አየንዴን፣ የአፍጋኒስታኑን ሐምበር ሆጃን ታላላቅ መጽሐፍቶችን አነበበ፤ ፈተሸ፤ መረመረ፡፡

የአፍሪካን የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች፤ የአንጎላውን የአጉስቲኖ ኔቶና የሞዛምቢኩን ሣሞራ ማሼል፤ የደቡብ አፍሪካውን ነጻነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላንና የኤ.ኤን.ሲን ትግል፤ የፈረንሣዩን ፓሪስ ኮሚዮን እና ዓለም አቀፉን የሠራተኛ መደብ እንቅስቃሴ፤ የታላላቅ ወታደራዊ ጠቢቦችን የቻይናውን ሣንትዙና ሌሎችንም የምሥራቁንና የምዕራቡን ፖለቲካል ኢኮኖሚና ፍልስፍና ጠልቆ ያነበበ፤ የመረመረ የእነዚህን ሁሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመፈተሽ ለኢትዮጵያ የሚበጀውን ትክክለኛ የልማትና የእድገት ጉዞ የቀየሰ ዋና መሐንዲስ ወደ ተግባርም የለወጠ ታላቅ ስብዕና የነበረው ሰው ነው፡፡

ግዙፉ የዓለም ፖለቲካ ትንቅንቅ የምዕራቡና የምሥራቁ ዓለም ቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃቱን፤ የሶሻሊስቱን ጎራ መዳከም፤ የኒዮ ሊበራል ኃይል በብቸኝነት ዓለምን መቆጣጠሩን ያስተዋለው መለስ ለኢትዮጵያ የሚጠቅማት ፖለቲካል ኢኮኖሚ የቱ ነው? የሚለውን ጥናትና አማራጮችን አማተረ፡፡

የዚህ ቁልፍ ጥያቄ መፈታት ዛሬ አገሪቷ ያለችበትን የልማትና የእድገት መንገድ ከፈተ፡፡ በግንባሩ ዋና ፀሐፊነት ሁሉንም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፤ የአገሪቱን የመከላከያ ፖሊሲና አወቃቀር የመቅረጽና የመምራት ድርጅቶቹንም አስተባብሮና አቀናጅቶ አገራዊ ፋይዳና ሥር ነቀል ለውጥ በሚያመጣ መስመር እንዲረባረቡ አደረገ፡፡

የኢትዮጵያ ምሁራን አብዛኛው የካፒታሊስቱንና የምዕራቡን ዓለም የፖለቲካ ኢኮኖሚ አወዳሽና አቀንቃኝ በመሆናቸው (ቀኝ ዘመም) ካፒታሊዝም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ዘመናት በቀውስ መናጡን በየአገራቱ 99 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ በድህነት፣ በችጋር፣ በሥራ አጥነት፣ በዘመናዊ ባርነት ሥር የሚኖር የጉልበት ሠራተኛ ነው፤ አንድ በመቶ ብቻ የደለበ ሐብት ባለቤት በመሆኑ ቀድሞ ከነበሩበት የኢኮኖሚ ቀውስ ዛሬም በከፋ ሁኔታ ከማይወጡበት አደጋ ውስጥ መዘፈቃቸውን እያስተዋሉም የሚደግፉት ይህንኑ ነው፡፡

እነዚህ በቡርዣው ፖለቲካል ኢኮኖሚ አፍቃሪነት የተጠመዱ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ጥቂት ሚሊዬነርና ቢሊዬነር ከበርቴዎች አብዛኛውን የአገሪቱን ሐብት ተቆጣጥረው

ሕዝቡን በሠራተኛነት ቀጥረው የሚያሰሩበትን፣ ሐብት የሚያከማቹበትን፣ ሕዝቡ ደግሞ ከድህነት ወደ ባሰ የድህነት አረንቋ የሚሄድበትን መንገድ አድናቂና ደጋፊ ናቸው፡፡

በቀጣዩ ዘመንም በዓለም ላይ የሚነሱት ሕዝባዊ አብዮቶች ዋነኛው መነሻ ምክንያት የኒዮ ሊበራሉ ከበርቴ ስግብግብነት ያስከተለው የሐብት ምዝበራና የብዙኃኑ በድህነትና በሥራ አጥነት ውስጥ መውደቅ መሆኑንም መለስ አስቀድሞ ለማስተዋል ችሏል፡፡

ስለዚህም ለኢትዮጵያ የሚበጃት በጣም በከፋ ድህነትና ኋላ ቀርነት ውስጥ የምትኖር፣ በረሀብና ድርቅ በተደጋጋሚ የተጠቃችና በዓለም አቀፍ እርዳታና እርጥባን ሥር የምትገኝ፣መሠረተ ልማቷ (መንገድ፣ ትራንስፖርት፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ፋብሪካ) ወዘተ በጣም ኋላ ቀር ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ለዚህ ፍቱን መድኃኒት የሚሆነው የአገሪቷን የተፈጥሮ ሐብትና የሰው ጉልበት በመጠቀም ዓለም አቀፍ ግንኙነትንም ጎራ ሳይለዩ ከሁሉም ጋር በወዳጃነት በመሥራት ለኢትዮጵያ የሚጠቅመውን ሁሉ መውሰድ፣ ታሪክን ቀይሮ ከድህነትና ከተረጂነት ለመውጣት ብቸኛው አማራጭ ልማታዊ መንግሥትነት መሆኑን መለስ አምኖበት ታላላቅ አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ፖሊሲዎች ቀርጾ ፓርቲው ወደ ተግባር እንዲለውጠው አደረገ፡፡

ኋላ ቀር ኢኮኖሚ 85 በመቶ በባህላዊ እርሻ ላይ የተንጠለጠለ ኢኮኖሚ፣ ጥቂት ፋብሪካዎች (ቀላል) የሆኑ ባለበት፣ ንገድ ያልተስፋፋበት፣ የጤና አገልግሎቱ ደካማ፣ የትምህርት ፖሊሲው በአብዛኛው በቀለም ትምህርት ላይ ብቻ የተመሠረተና ሦስት ዩኒቨርሲቲዎች፣ ጥቂት ኮሌጆች፣ የተወሰኑ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ያሏት አገር፣ነጋዴው ከሸቀጥና ከአነስተኛ ሆቴል ንግድ ግፋ ቢል ከሉካንዳ ያልወጣበት፣ አገሪቷ ብዙ የተፈጥሮ ሐብቶች፣ ድንግል መሬት፣ የውኃና የማዕድን ሐብት ቢኖራትም ምንም ያልተጠቀመችበት በመሆኑ በተለየ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ሥር ነቀል መንገድ ካልተሄደ በስተቀር ለውጥና እድገት ማምጣት የማይቻል መሆኑን መለስ ጠንቅቆ ተረድቶታል፡፡

ይህ ብቻ ሳይሆን ለረዥም ዘመናት በውስጥና በውጭ ጦርነት ኢኮኖሚዋ የደቀቀ በመሆኑ ከጎረቤት መንግሥታትና በዓለም አቀፍ ደረጃም አገሪቷን ሙሉ በሙሉ የሚለውጥ የውጭ ፖሊሲም አስፈላጊ መሆኑን አምኖበታል፡፡

በዚህም መሠረት የአብዮታዊ ዴሞክራሲን (የልማታዊ መንግሥት) መርህ ለኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ መሆኑን አምኖበት ከፓርቲው ጋር መክሮና ዘክሮ አፅድቀውት ወደ ተግባር ተሸጋገረ፡፡ ሲያስቡት የማይሞከር፣ የማይደፈር፣ የማይቻል፣ የሚያስፈራ የነበረውን ታላቅ ድፍረት ቁርጠኝነትና ውሣኔ የሚጠይቀውን አገራዊ የልማትና የእድገት እርምጃ ወደ ተግባር ለወጠው፡፡

በኢኮኖሚው መስክ መለስ የተከተለው ፖሊሲ ከፊሉ በመንግሥት እጅ (ቁልፍ የሆኑት) እንዲያዙና እንዲመሩ ሌላው በነጻ ገበያ መርህ በመሥራት የአገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስተሮች እንዲሳተፉበት ሲደረግ ይህም ከኒዮ ሊበራሉ ዓለም አቀፍ ኃይል፤ ከለጋሾቹ ወርልድ ባንክና አይ ኤም ኤፍን ከመሳሰሉት ዓለም አቀፍ አበዳሪዎች የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ ሊበራላይዝድ ሆኖ በግል ባለሐብቶች እጅ መግባት አለበት እንጂ በመንግሥት የሚመራ ኢኮኖሚ መኖር የለበትም ሲሉ ተቃወሙ፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ መብራት ኃይል፣ ቴሌ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሁሉም ለግል ባለ ሐብቶች ለውጭ ኢንቨስተሮች ጭምር መሸጥ አለበት ሲሉ ተከራከሩ፡፡ መለስ ይህንን አምርሮ ተቃወመ፡፡ እነዚህ ከአገር ህልውናና ደህንነት ጋር የተያያዙ ስለሆነ በኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ እጅ ይሆናሉ፡፡ አይሸጡም፤ አይለወጡም አለ፡፡ እነርሱም እስከ ዛሬ ቂም እንደያዙ ቀሩ ፡፡

የአገሪቷን ሐብት ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠርና ለመመዝበር ባለው ፍላጎት ዓለም አቀፉ የኒዮ ሊበራል ኃይል በየአገሩ እነዚህን ተቋማት የግሉ ሐብት አድርጎ በመግዛት መያዝ ይፈልጋል፡፡ይህንን አስተሳሰብ የሚደግፉ የኒዮ ሊበራል የፖለቲካ መስመር የሚያራምዱ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በዲያስፖራ የሚገኘውን ጽንፈኛ አክራሪ ኃይል ጨምሮ የሚራወጡት አጠቃላይ የአገሪቷን ሐብት ለዓለም አቀፍ ከበርቴ የካፒታሊስት ኃይሎች አሳልፈው ለመስጠትና ሙሉ በሙሉ ዘመናዊ የካፒታሊስት ባርነት በጫንቃቸው ላይ ለመጫን ነው፡፡ ይህ ደግሞ መቼም እንደማይሆን መለስ አረጋግጦላቸዋል፡፡ ሕዝቡም የአገሩና የሐብቱ ባለቤትና ባለመብት ተጠቃሚም በመሆን ይቀጥላል፡፡

መለስ አገሪቷን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ከተረጂነት በማላቀቅ ለራሷ የበቃች እንድትሆን ከተረጂነት እንድትወጣ፤ የጥንት ገናና ክብሯና ስሟ እንዲመለስ በኢኮኖሚው መስክ የቀየሳቸው ታላላቅ ውጥኖች በአምስቱ ዓመት መሪ እቅድና የትራንስፎርሜሽን ፕላንም

ውስጥ የተካተቱ ናቸው፤ እነዚህም ሙሉ በሙሉ ችግሮችን እያስወገዱ አቅም እያጎለበቱ በስኬት ጎዳና ወደ ግባቸው እየተመሙ ይገኛሉ፡፡

ዜጎች በተለይም የተማረው ወጣት ኃይል በሥራ ፈጠራ፤ በአዲስ ቴክኖሎጂ አመንጪነት፤ በርካታ የእደ ጥበባት ሥራዎች የሚያስፋፋና የሚያጎለብት፤ ጥቃቅንና አነስተኛ የነበሩትን ወደ ኢንተርፕራይዝ መካከለኛና ከባድ ኢንዱስትሪዎች የሚያሸጋግሩበት ሥልት ነድፎ ውጤታማ እንዲሆን በማድረጉ ዛሬ በርካታ ዜጎች የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው የሐብት ባለቤት በመሆን ለሌሎችም የሥራ እድል እየፈጠሩ ይገኛሉ፡፡

መለስ የኖረባቸው 57 ዓመታት ምናልባትም በአገሪቱ ከተገኘው ሥር ነቀል የኢኮኖሚና የእድገት ለውጥ አንጻር ሲመዘን በመቶ ዓመታትም ከዚያም በላይ የሚመነዘር ይሆናል፡፡ ዘመናዊና ደረጃቸውን የጠበቁ መንገዶች ግንባታ፤ የቀለበት መንገድ፤ የሕዝቡን የቤት ችግር የሚፈቱ ኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ በመላው አገሪቱ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

ከዚህም ጋር የነበሩትን ሦስት ብሔራዊ ዩኒቨርሲቲዎች ከ32 በላይ ማድረስ፤ የጤና አገልግሎቱን በመላው አገሪቱ ሩቅ ቦታዎች ማዳረስ፤ የኤች አይ ቪና የእናቶች ሞት መቀነስ፤የትምህርት አገልግሎትን ከከተማ ሩቅ ገጠር ማስፋፋት፤ አርብቶ አደሩን የመስኖ ልማት ተጠቃሚ ማድረግና የተረጋጋ ኑሮ እንዲኖርና እርሻ እንዲለምድ ማስቻል፤ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የመብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ የቻለ ነው፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት በርካታ በዓለም ደረጃ ታዋቂ የሆኑ በአፍሪካም የሌሉ የድሪም ላይነርና የዘመናዊ ንግድ መርከብ ባለቤት፤ የዓለም አቀፍ ሽልማት ተደጋጋሚ አሸናፊዎች ለመሆን የበቁበትን ፖሊሲ በሥራ ላይ እንዲውል እቅዱን የነደፈው ለታላቅ ውጤትም የበቁት በመለስና በፓርቲው አመራር ነው፡፡

መለስ በርካታ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ መሪዎች ደግመው ደጋግመው እንዳረጋገጡት ሁሉ በእውቀት የገዘፈ የመጠቀ ብስል የላቀ የአመራር ብቃት ነበረው፡፡ የትኛውንም ዓይነት ችግሮች በብቃት የማጤንና መፍትሄ የመስጠት ልዩ ክህሎት የነበረው፤ ሁሌም አዳዲስ ሀሳቦች የሚያመነጭ፤ ተሟጋችና ተከራካሪ አንደበተ ርቱዕ፤ በተጨባጭ የማሳመን ችሎታው የላቀና የመጠቀ በእርግጥም በተባበሩት መንግሥታት የአሜሪካን አምባሣደር የነበረችው ሱዛን ራይስ እንዳለችውም በዓለም ደረጃ የሚመደብ መሪ ነበር፡፡ መለስን

የተነጠቀችው ያጣችው አገሩ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን በዓለም ደረጃ ወክሷት ቆሞ ለአንድ ቢሊዮን ሕዝቧ የተሟገተላት አፍሪካም ዓለምም ጭምር ነች፡፡

በመለስ ራዕይና የአመራር ዘመን በነበረው ልዩ ብቃትና ችሎታ ጥንት ኢትዮጵያ የነበራትን ክብር ወደ ቦታው ለመመለስ ያደረገው ትግል ተሳክቶለት የአፍሪካን ሕብረት ዋና መቀመጫ ከአዲስ አበባ ለማስነሳት ተጠንስሶ የነበረውንም ሴራ ሙሉ በሙሉ አክሽፎታል፡፡ ቀደምት የኢትዮጵያ መሪዎች በአገራቸው ውስጥ ችግር ቢኖርባቸውም ለአፍሪካ ነፃነትና ክብር የማያወላውል ቁርጠኛ አቋም የነበራቸው መሆኑን ገልፆ ፅህፈት ቤቱ አዲስ አበባ እንዲፀና፤ አዲስ አበባም የአፍሪካም የዓለምም የዲፕሎማቲክና የፖለቲካ መዲና ከብራስልስ በመቀጠል እንድትሆን ያስቻለ ብስል ዲፕሎማትና ታላቅ መሪ ነበር፡፡

በዘመናዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ዝርጋታና ግንኙነትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰለጠነው የዓለም ሕዝብ እኩል የሞባይል ቴሌፎን ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረጉ ዛሬ የተገልጋዩ ቁጥር 28 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ ሩቅ ገጠር አካባቢዎች ገመድ አልባ ስልክ፣ ሞባይል፣ መብራት እንዲደርስም ተደርጓል፡፡ በእርግጥ ብዙ ቢቀርም በሂደትና በእድገት እንደሚደረስበት አያጠራጥርም፡፡

በአገሪቱ የፕሬስ ነጻነት መታወጅ፤ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መፈጠር፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በህገ መንግሥቱ መሠረት በሠላማዊ መንገድ ተደራጅተው መንቀሳቀሳቸው፤ በሠላማዊ የብሔራዊ ምርጫ ውድድር እንዲሳተፉ መደረጉና ፓርላማ መቀመጫ አግኝተው መግባታቸው፤ የግል ራዲዮ ኤፍ ኤም ጣቢያዎች መከፈት፤ አንድ የነበረው የአገሪቱ የቴሌቪዥን ቻናል የተለያዩ ቻናሎች መፈጠር፤ ክልላዊ መንግሥታትም የየራሳቸው የቴሌቪዥንና ራዲዮ ጣቢያ፤ የኮሚኒቲ ራዲዮ አገልግሎት ባለቤትም ለመሆን መቻላቸው እነዚህም የመለስና የፓርቲው ራዕይ ውጤቶች ናቸው፤ ከዚህ በፊት በአገሪቱ ታሪክ ውስጥ ያልነበሩና ያልታዩ ናቸው፡፡

መለስ ኢትዮጵያ ራሷን ከማንኛውም የውጭ ጥቃት በብቁ ሁኔታ መከላከል የምትችልበትን ብሔራዊ ወታደራዊ ስትራቴጂና ሚሊተሪ ዶክትሪን ምርጥ ከተባሉት የዓለማችን አደረጃጀቶች ቀምሮ በማውጣት በዘመናዊ ትምህርት፣ በቴክኒክ፣ በወታደራዊ ሣይንስ ጥበብ የበቃ ግዳጆችን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ በብቃት ለመወጣት የሚችል ተዋጊና አምራች የሆነ ሠራዊት እንዲገነባ አድርጓል፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ቀድሞ ከነበሩት ጥቂት ትምህርት ቤቶች አልፎ የዩኒቨርሲቲና ኮሌጆች ባለቤት እንዲሆን አስችሎታል፡፡ የቴክኒክ፣ የሙያ፣ የሕክምና፣ በየደረጃው የመስመራዊ የከፍተኛና የጄነራል መኮንኖች ስታፍ ኮሌጆች ባለቤት በመሆን ከውጭ አገራት የሚመጡ መኮንኖችም በኢትዮጵያ አካዳሚዎች እየሰለጠኑ ተምረው ይሄዳሉ፡፡ መከላከያው ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች፣ ጥይቶች፣ ትጥቆች፣ ተሸከርካሪዎች፣ ትራክተሮችና ሌሎችንም የሚያመርትበት አቅም ገንብቷል፡፡

ቀደም ሲል አገሪቷ በውጭ ምንዛሪ ከውጭ የምታስገባቸውን ራሱ ማምረት የቻለበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ሠራዊቱ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለዓለም አቀፍ የግዳጅ ማስከበር ተልዕኮ በብቃትና በግዳጅ አፈጻጸሙ ተመራጭ መሆን ችሏል፡፡ ለአገሪቱ መንገድ ድልድይ ግድብና ለመሳሰሉት  ግንባታዎች ብረት የሚያቀርበው ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ መፈጠር ግዙፍ ስኬት እያመጣ ሲሆን ይህም የመለስ ራዕይ ውጤት ነው፡፡

መለስ ከሰራው በላይ ብዙ ሊሰራ የሚችል አቅም እያለው የህይወት ጉዞው ቢገታም ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ እድገትና ልማት ያበረከተው አቅጣጫ መሪ የፖሊሲና ስትራቴጂ እቅድ የማይቻለውን ሁሉ እንዲቻል አድርጎ፤ ሕልም የነበረውንም የአባይ ወንዝ ለመገደብ መሠረት ጥሎ፤ ካለማንም የውጭ እርዳታ በኢትዮጵያ ሕዝብ ጉልበት አቅምና ገንዘብ እንዲገነባም ወስኖ ወደ ተግባር የለወጠ ድንቅና ታላቅ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

የመጠቀው አስተሳሰቡና ብሔራዊ ራዕዩ ከትውልድ ትውልድ እየገዘፈና እየደመቀ ይነጉዳል እንጂ ከቶውንም አይገታም፤ አገሬ ለምታ አድጋ ከድህነትና ከተረጂነት ከተመጽዋችነት ወጥታ ማየት እፈልጋለሁ የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያወድሰዋል እንጂ አያነውረውም፡፡

መለስ የኢትዮጵያን ባህር በር ሰጠ፤ አስወሰደ ለሚሉትም ጭፍን ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ታላቅ ትምህርት ሰጥቷቸው አልፏል፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ ያደገችው፣ የለማችው፣ የተለወጠችው ሠላም አግኝታ ስለሰራችና የባህር በር ባይኖራትም የባህር በር ተከራይታ እየሰራች ባለችበት ሁኔታ ነው፡፡ መለስ ያለ ባህር በርም ታላቅ እድገት ማምጣትና አገርን መለወጥ እንደሚቻል በተግባርና በተጨባጭ አሳይቷል፡፡

በአገር ውስጥ ደረቅ ወደቦች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡ የባህር በር በነበረን ወቅት ጭርሱንም ያልታዩና የማይገመቱ፣ የማይታሰቡ ታላላቅ ለውጦች ናቸው የመጡት፡፡ በሻዕቢያና

በኢሣያስ አፈወርቂ በኩል የነበረውን የሁለት ወደብ አለን ካለ እኛ ኢትዮጵያ አታድግም፣ ጉሮሮዋን አንቀን እንይዛለን፣ የትም አትደርስም የሚለውን ድንፋታና እብሪት ያለወደብም ማደግ እንደሚቻል በማሳየት መለስ አንኮታኩቶ ጥሎታል፡፡ እኛ ካልተጠቀምንበት አሰብ የግመል ማጠጫ ያ ነው የሚሆነው እንዳለውም ሆኗል፡፡

በእርግጥ አሁን ኢትዮጵያ ባለችበት አመርቂ እድገትና ልማት የራሷ ወደብ ቢኖራት ለወደብ ኪራይ የምትከፍለው ወጪ ለሌሎች ልማቶች ሊውል ይችል የነበረ ቢሆንም ወደብም ሳይኖር ኪራይም ተከፍሎ አሁን የተደረሰበት እድገት ላይ መደረሱ አገር በቁርጠኝነት ለሥራ ከተነሳች ብቃትና ራዕይ ያለው አመራር ካላት የትኛውንም መሰናክል አልፋ ለትልቅነት ከመብቃት የሚያግዳት ምንም ነገር እንደማይኖር የመለስ ራዕይና አመራር ታላቅ ማሣያ ነው፡፡ለተተኪውም ትውልድ ትልቅ ትምህርት ነው፡፡

ጦርነትን አንፈልግም፣ ጦርነታችን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ከረሀብና ከድርቅ ጋር ነው፣ አንገት አስደፊ የሆነውን ድህነት ተረኛነትና ምጽዋት ጠባቂነት ለተተኪው ትውልድ አናወርስም የሚለው መለስ በእርግጥም አገሪቷንና ሕዝቧን ታላቅ የሆነ የልማትና የእድገት ጎዳና መስመርና ራዕይ አስጨብጧቸው ነው ብዙ ሊሰራበት በሚችለው እድሜው ያለፈው፡፡ይህንን የገዘፈ ራዕይ ከዳር ማድረስ አገሪቷን በሰለጠነ ሁኔታ ማልማትና ማሳደግ ከእንግዲህ የተተኪዎችና የ90 ሚሊዮን ሕዝብ ኃላፊነትና ግዴታ ነው፡፡

አዲስ አበባ የዘመናዊ ባቡር አገልግሎት ተጠቃሚ ሆና ክልሎችም ድረስ የሚያስተሳስር ፈጣን የባቡር አገልግሎት በቅርብ ዓመታት እንደሚኖር ስናስብ ኢትዮጵያ በወርልድ ባንክ፣ በአይ ኤም ኤፍ እና በሌሎችም ዓለም አቀፍ ተቋማት እንደተመሰከረላት ሁሉ በሰብ ሰሀራ አፍሪካ አንደኛዋ በፈጣን ኢኮኖሚ እድገት ላይ የምትገኝ አገር መሆኗ፣ የተረጋጋ ሠላም ያላት፣ለኢንቨስተሮች አመቺና ተመራጭ፣ የቱሪስት መዳረሻ የመሆኗና የማደጓ፣ የመለወጧ ቁልፍ ምስጢር መለስና የመለስ ራዕይ የፓርቲው ራዕይ መሆናቸውን ለመረዳት አይከብድም፡፡

መለስ ቢያልፍም ለአገሩና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ መሆን የነደፈው የቀየሰው ራዕይ በከፍተኛ ብቃትና ጉልበት ይቀጥላል፣ አይስተጓጎልም፡፡ አገሪቷ በሙት መንፈስ ነው የምትመራው ለሚሉት ህሊናቸው በቁማቸው የሞቱ ሙቶች፣ በመለስ የእውቀትና የሥራ

መንፈስና ራዕይ ከኢትዮጵያ አልፎ ድፍን አፍሪካና ታዳጊውም ዓለም ጭምር እየተረባረቡ እየሰሩበት ለውጥም እያመጡበት መሆኑን ሊረዱት ይገባል፡፡

መለስ በሕይወት ባይኖርም ከኢትዮጵያም አልፎ ለአፍሪካ የተረፈ ከድህነት ወጥተው ለማደግም እየተከተሉት ያለ ህያው መንፈስ ነው፡፡ የመለስ አገርን የማልማትና የማበልፀግ መንፈስና ታላቅ ራዕይ የማይናድ ግዙፍ ተራራና የማይፈርስ አለት ነው፡፡ ተጨልፎ የማያልቅ ባሕርና ውቅያኖስ ነው፡፡ ስሙም በአፍሪካም በዓለምም የተተከለ ከሚጠቀሱትና ከሚታወሱት ጥቂቶቹ ውስጥ ይጠቀሳል፡፡